# ዝክረ - ጥበብ

## Arts Memorandum




# አዳም ረታ የአነ ጽሁፍ ዘውግ

አብሮነት - ነጻ ራዕይ ቅፅ. ፮

ውድ አንባቢያን፤

በጁን 2012 ዕትማችን ላይ ከደራሲ አዳም ረታ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ የመጀመሪያ ክፍል እንዳቀረብን ይታወሳል። ደራሲ አዳም ረታ ማህሌት፣ ግራጫ ቃጭሎች፣ ከሰማይ የወረደ ፍርፍር፣ አለንጋና ምስር፣ እቴሜቴ ሎሚ ሽታ፣ ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ እና በገናና ህማማት የተሰኙ ድንቅ መጽሃፍትን የፃፈ ሰው ነው። በዚህ ዕትማችን ሁለተኛውንና የመጨረሻውን ክፍል የሆነውን ታነቡ ዘንድ በደስታ እንጋብዛለን።

**ቱብሮኘነት፦ በስኬታማ ደራሲነት አይን ሲታይ በውጪ አገር እየኖሩ በተነጻጻሪ ርቀት ላይ ሆነው ስለ ማኅበረሰብ የመጻፍ ተግዳሮት እና ጸጋ ምን ይመስላል?**

ስኬታማ ደራሲ ለተባለው፤ አንፃራዊነትን ለሚንከባከቡ፣ ከጥናትም ይሁን ከግል ስሜትና ፍላጎት ተነስተው ለሚፈርዱ፣ ወይም ለሚያደሉ ቦታውን ብለቅ ይሻላል። ስኬታማ የሚለውን ቃል ሙሉ ፍቺ አይናአፋር የተጠየቀ ቅንፍ ውስጥ ልክተተው።

ስኬታማነት ተነቃናቂ ኢላማ ነው። ማታ ላይ አጠናቅቄ በሰራሁት ድርሰት ረካሁ ብዬ ብተኛም፣ ሲነጋ ቅር የሚሉኝ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ከአመታት በፊት በፃፍኩት ዛሬ ላልደሰት እችላለሁ። የስኬታማነት መለኪያዎች አስራ አስር ናቸው። ነገር ግን አንድ ሰው አገሩ ውስጥ መኖሩንና ወይም አለመኖሩን የስነፅሁፍ ስኬታማነት መገምገሚያ ማድረግ ምስፋርን/ስፍራን (place) ብቻ የብቃት መለኪያ ማድረግ ነው። ይሄ ነጠላ ብቆታ በአብዛኛው ከውጤቱ ወይም ከድርሰቱ ውጭ ያለ ነው። የተለያዩ የስፍራ መደቦች አሉ፤ የግል ስፍራ አለ (personal space)፣ የቤትህ፣ የቀበሌህ ስፍራ፣ ወዘተ... እያለ በተጨማሪም ደራሲው በኢምንትነቱ የሞሎኩሌው ወይም የወተትማው መንገድ አባል ነው። ግንባሩ በሶላር ፍሌርስ ይግላል፣ በበጋ በሚመጣ ዝናብ የሚከረስስ ቆዳ አለው። በምድር የመግነጢስ መረብ ይረግባል፣ ይወጠራል።

የአንድ ደራሲ ዋናው መሳሪያው ምናቡ ነው። ግን ነባር ልዩ ቦታህ በነበርክ ጊዜ በስር-ነቀል ልምድ ውስጥ እንድታልፍ ደንብ መሰለኝ (ይሄ ልምድ ፖለቲካ ብቻ መሆን የለበትም። ብዙ ጊዜ አንድ የልምድ ዝርያ ላይ ብቻ በማተኮርና ለዛም የማይገባውን ክብደት ብቻ በመስጠት በልምድ የመብሰል መለኪያ ሊደረግ ይሞከራል። ይሄ አድልዖ ነው)።

ትተኸው (በእርግጥ ትተኸዋል ወይ?) የሄድከው ህብረተሰብ ውስጡ ምን ይመስል እንደነበር በመጠኑም ቢሆን መረዳት አለብህ። የትኛው ክስተትና ዕውነታ ነው ውዝፍ? (constant) የትኛው ነው ተለዋዋጩ? የቱ ነው ፈዞ/ተለውጦ የሚጠብቅህ? አለዋወጡን የሚገዙት የግንጽሊት ንጥረ ነገሮቹ (elements of metamorphosis) ምንድናቸው? ወዘተ...

> ብዙ ብሑት (innovators) የሚባሉ የባዕድ ደራሲዎች ትልልቅ ድርሰቶቻቸውን የፃፉት ከትውልድ አገራቸው ውጭ ሆነው ነው። እንደውም አንዳንዴ ስለራሳቸው አገር በጠለላቸው አገር ቋንቋም ይፅፋሉ። ወሳኙ ያሳለፍከው የልምድ ስፋትና ጥልቀት፣ ለዛም ያለህ ግንዛቤና በንቁነት ወይም በኢ-ንቁነት የምታነሳቸው ንፅፅሮች ናቸው እንጂ አካላዊ ዕርቀትና ቅርበት መለኪያ አይደለም።

በራስህ ከምትገነዘበው፣ ተገንዝበህ የምታሰላስለው፣ አሰላስለህ መደምደሚያ የምትወስደበት፣ አንድ ተራ የመሰለ ድርጊት/ገጠመኝ ሰዎችን በግል ብቻ ሳይሆን ስርአት ውስጥ ያላቸውን ባህርይ እንድትረዳ ሰፊም ይሁን ጠባብ መንገድ ይከፍትልሃል። በስደት ስኖር በእርግጥ አዲስ የረቀቀ የስነፅሁፍ መሰረተ-ልማት (Infrastructure) ውስጥ እገባለሁ። እነዛ መኖራቸውን ታያለህ፤ ግን ለእኔ ስራ መመጠናቸውን ማመዛዘን አለብኝ። ንፅፅር የምለው ይሄንን ነው።

ባዕድ አገር ሆኜ ኢትዮጵያ ውስጥ ስላለ የቄስ ትምህርት ቤት ዘመን ብፅፍ በግል ተዘክሮዬ ይገፔው የመጣሁት የመረጃ ወይም የዕውነታ አንኳር አለ። ዝርዝሩ ምናብ ነው። ጥቂት የሚታወሱ ነጥቦች አንስተህ እነዛን ሚዛን በመጠበቅ የማያያዝና ጊዜ-ዘላይ ጭብጥ የማስነከስ ነው። ከልጅነቴ አርባ ዓመታት እርቄአለሁ በሚል ስለ ልጅነት ልብወለድ የመፃፍ መብቴን አላነሳም። "የተወለድኩት አዋሳ ነው፣ አዲስአባ መጥቼ ለምን ስለአዋሳ እፅፋለሁ?" ብዬ በቦታ መሸጋሸግን ወሳኝ አላደርግም (በአገር ውስጥ ስደት)። ይሄን መሰረታዊ ነጥብ ሃያሲው ከሳተ የቀረበው ትችት ሳይሆን ስህተት ፍለጋ ነው። የልጅነታችንን ቦታዎችና ጊዜዎች ኢትዮጵያ ውስጥ እንኩዋን ብንሆን ሁሉንም ትተናቸው ሄደናል። ሁሉም ደራሲ ላለፈው ዘመንም ይሁን ቦታ/ስፍራ በሆነ ደረጃና መልክ ባዕድ ነው። ቦታዎችም እንደ ሰው ይለወጣሉ። እንደ ደራሲው እንደራሱ እና እንደ ገፀባህርያት። ልብወለድ ዶኪመንታሪ አይደለም።

ቱብዘኘነት፦ ለፈጠራ ስራዎችህ የበተለይ ወይም አይነተኛ አስተዋፅዖ የሚያደርግ ልዩ ነገር/ሁኔታ/አጋጣሚ/ምክንያት/ፍጥረት/ እንዲሁም የምትከተለው ልምምድ/ስልት አለ? እንዲሁም ርዕሶችህና ስራዎችህ የሚሰናኙበት ልዩ የሚባል መንገድስ?

የተወሳሰቡ ልምዶች አሳልፌአለሁ። በእኔ የተፈጠሩ ወይም በሌሎች የተሰጡኝ። (ምርቃትም ይሁን እርግማን) አስከፊም ይሁን ደስ የሚሉ። እነዚህን ልዘረዝርልህ አልችልም። ብዙም ናቸው፤ ጥቂትም ናቸው።

በባህርዬ በደንብ አያለሁ። አድልዖ አላደርግም። ይሄ ሁኔታዎች በነፃነት ለእኔ እንዲከሰቱ ያደርጋል። በጣም የሚሞቅ ፀሐያማ ቀን ባልወድም ፀሐይ ውስጥ እቆማለሁ አለመውደዴን አጠናለሁ። እሱንም አወጣና አወርደዋለሁ። የሆነ የዜን ዝንባሌ (Zen attitude)እይዛለሁ። ያለ ይሉኝታ (ምን መሆኔ ነው? ሰዎች ምን ይሉኛል?) ሳልል ለማየው ህያው ወይም ጎፍ (physical) አለም ራሴን በመስጠት ነው። ቅን መሆን አለብህ። ይሄን ደሞ አስበህ አታመጣውም (የሚያደርጉት ይኖራሉ)። ጥንቁቅ አይደለህም። ዕቅድ የለህም። መረጃዎችን ብቻቸውን ሳይ (መገንዘብ) ከፍፁም ግኑኝነት አርቃቸዋለሁ ማለትም አይደለም። ያኔውኑ በፍጥነት ሊከሰትባቸው የሚችሉ አውታሮችን አስባለሁ፣ ወይም በትካቴ ይመጣሉ። በቀለ የተባለ ረኸዋም ልጅ ስልክ እንጨት ሊያስታውሰኝ ይችላል። ስልክ እንጨቱን ሳይ በቀለ ትዝ ሊለኝ ይችላል። አልማዝን ሳይ ቄጤማ ትዝ ሊለኝ ይችላል፣ የትርሲትን ድምፅ ስሰማ ሚጥሚጣ፣ ቁሶቹን ሳይ ደሞ አልማዝና ትርሲት። ዝርው የመሰለው ነገር በተለዋጭና በንፅፅር ስርአት ውስጥ ይገባል። ነጠላነትና ውህድነት በአያኖነት ይተገበራሉ።

የመገንዘብ አድልዖ (Cognitive bias) ብዙ ነገር የመፃፍ ግላዊ ነፃነትህን ሊጋፋ ይችላል። በእኛ አገር ያልተነገረለት ሳንሱር ይሄ ነው። አንዳንድ ጊዜ ወሳኝም ይሆናል። እነዚህ በእንግሊዘኛው ተሳፋሪነት (Bandwagon effect)፣ የጥማድ ህልዮ (Group think)፣ የጂም ባህርይ (Herd behavior)፣ ምናምን የሚባሉ ናቸው:: ይሄ ወደ ስሜት ህዋስ አድልዖ (Observational bias) ወይም የፅንሰ ሃሳብ አድልዖ (Conceptual bias) ይወስዳል::

ብዙ ሰው ስለሚያደርገው ላድርገው ብዬ ማድረግ፣ ያለ ዝርዝር ብቆታ መርጩ ማየት፣ እኔ ነገሩ ገብቶኛል ብዬ ከመጀመሪያው የማየውን ነገርና የምሰማውን ወስኜ በራሴም ይሁን በሌሎች ትርጓሜ መጥኜ ማስቀመጥና የግል/የቡድን እሴቴን ወይም ሕልዮዬን የማየው/የምገነዘበው/ ጉዳይና ነገር ላይ በጫና ማሸጋገር ከእውነታው ስለሚያሸሹኝ አልጠለልባቸውም። ሁሉ ነገር ለደራሲ መረጃ ነው። መረጃ ስል በተጨባጭ የማየው (በራሴ የስሜት ህዋሶች)፣ ከሰው የምሰማው፣ የማነበው፣ በህልሜ የማየው፣ የምቃዠው ሊሆን ይችላል። ለእኔ ክብደትና መራሂነት ያለው የመጀመሪያው ነው።



አንዳንድ የመረጃ አንኩዋሮች ጥቅጥቅ ሊሆኑ ይችላሉ። እሴታቸው ቸኩሎ ላይከሰት ይችላል። ዛሬ ያነጫነጨኝ ልምድ ነገ ሊያስቀኝ ይችላል። ትናንት አደገኛ ያልመሰለህ ልምድ ቆይቶ አደገኛነቱ ይከሰታል። ዛሬ አደገኛ የመሰለ ልምድ ነገ ምቹ ሊሆን ይችላል። የአንዳንዱ ተራ የመሰለ ተፅእኖ ወደ ድንጋግ የለሽ (ዳርቻ የለሽ) መረጃ ሊፈነዳ ይችላል። የማደርገው ከፈነዳ በኋላ የተበታተኑ የኩነት ፍንጣሪዎችን ወይም ዛላዎችን በማያያዝ መስራት ነው።
ይሄን የአፃፃፍ ስነ-ግብሬን (Method) ሕፅናዊነት እለዋለሁ። የምናገርለት ጉዳይ በእኛ አገር አዲስ ቢሆንም በሌሎች አገሮች የተሰራበት ወይም እየተሰራበት ያለ ሊሆን ይችላል። በዛ በኩል በሰፊው በሰፊው ልናገርለት የምችል የአለቃ ግንዛቤ የለኝም። ግን የአፃፃፍ ስልቴን ከመግለጫዎች በፊት በድርጊት ለማምጣት ሞክሬአለሁ። ይሄም የራሱ መሰረት አለው። በ"ግራጫ ቃጭሎች" መግቢያ ላይ የሞከርኩት መንደርደሪያ ቢሆንም ቦታው እንዳልሆነ የተቹኝ አሉ። የሆነ እውነትነት አለው። ምናልባት ቆየት ብዬ ስለ ስነ-ግብሬ በሆነ መልክ ለአንባቢያን ለብቻው ማቅረብ እንዳለብኝ አምናለሁ።

መግለጫ (ማኒፌስት) ስትሰራ ወደ ሕፅናዊነት ውስጣዊ አስተጋባኢ (Essence) ለመድረስ ዲበ-አካላዊና አእምሮአዊ ኑባሬ (Metaphysiclal and Ontological) ጥናቶች ያስፈልጋሉ። አፅንኦትም የሚያገኘው እንዲያ ነው እንጂ አዲስ አፃፃፍ ነው ብዬ ድርቅ ስላልኩ

አይደለም። ሃያሲያንም የቻሉትን እየወረወሩ የፀዳ የአእምሯዊ ኑባሬ ቅኝት በመስራት የሕፅናዊነት ትግብርትን ሊደግፉት ወይም ሊነቅፉት ይችላሉ። እኔ በተመጠነ ደረጃ በፅሁፍ ወይም ስርአት ባለው መንገድ ግልፅ ባላደርገውም ሕፅናዊነት አንዳንድ የሚያዋጣ አቅጣጫ ሊይዝ እንደሚችል ከፍንጭ በላይ መከራከሪያ አለኝ። አንዱ ድርጊቱ ነው። "ግራጫ ቃጭሎች"፣ "እቴሜቴ ሎሚሽታ" እና "ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ" ድርጊቶቹ ናቸው።

ብዙ ጊዜ ይሄ ገጠመኝ ውስጥ ሁኔታዎች እስኪዶሉኝ ከልብወለዴ ጀርባ ምን አይነት ፍልስፍና እንዳለ ጠይቄ አላውቅም። የ"ግራጫ ቃጭሎች" መዝገቡ ስለዲበ-አካል ግድ ሊሰጠው አይችልም። እትዬ ብርቄ ስለ ሕልውናዊነት (Existentialism) ልታነሳባቸው አትችልም። አንዳንዴ ሰዎች ሲጠይቁኝ ግን እንደ አንድ ደራሲና ግለሰብ ጉጉት ጥሎብኝ ያልፋል።

በተጨማሪም ኮስታራ ከሆነ ወይም የተባ የስነ ፅሁፍ ወይም የባህል ሂስ ካለበት ህብረተሰብና፤ ልብ ወለዱ እንኳዋን ንኡስ ዘውጎች ያልተሰየሙለት ዘመናዊ ከተባለ የስነ-ፅሁፍ ባህል የተመዘዝኩ ነኝ። ይሄ እጥረት በሆነ መልክ ድጋፍ ያጣሁ ደራሲ ያደርገኛል። የራሴን ፍልስፍና ስናገር በአገራችን የመፃፍ ካርታ ላይ ከማንና የትጋ እንደምታስቀምጠው ግራ ሊያጋባ ይችላል። ይሄ ባይተዋርነት ሆነ ተብሎ ከሚሰነዘር አግላይነት ጋር ሲደመር ሕፅናዊነት የሚለው ቃል ገቺ ወይም አጋጅነት ይኖረዋል።

ወደ ሕፅናዊነት የገፋፉኝን ሁለት ቀላል ገጠመኞች ላንሳ።

ሀ/ በመፃፍ ድርጊት ላይ ያጋጠመኝ ችግር፡- አንድ ተራ የመፃፍ ሂደት እንደ ምሳሌ ላንሳ። በቀለ የሚባል ገፀ ባህርይ የአጥር በር አልፎ የቤቱ በር ይደርሳል፣ ልክ በሩ ጋ ሲደረስ ያንኳኳል (አንበል)። 'ታ-ታ-ታ-ታ-' በቀለ በሩን አንኳኪ ስል ለመሆኑ ልክ ነኝ? '-ታ-ታ-ታ-' በሩ ጋ ቆሞ ሊያንኳኳ ሲል ከኋላው የሆነ ሰው ቢመጣስ? 'ታ-ታ-ታ-ታ-' በግራ በኩል የሆነ ውሻ እየሮጠ ቢመጣስ? 'ታ-ታ-ታ-ታ-' መስኮት ተከፍቶ ስላየ ከማንኳኳት ይልቅ በመስኮቱ በኩል ሰው ሄጄ ልጥራ ቢልስ? እነዚህ ምርጫዎች ትክክል ቢሆኑም እኔ በሩን ከፍቶ እንዲገባ አደርጋለሁ። ለምን አደርጋለሁ? አንዱ መረጃ ወይም የሴራ መስመር (Plot line) ከሌላው የቀደመበት የብቆታ መለኪያው ምንድነው?

ከላይ የጠቀስኳቸው ነጥቦች (የውሻው ሊናከስ መምጣት፣ የተከፈተው መስኮት... ወዘተ) ከጀርባቸው ሌላ ታሪክም ሊኖራቸው ይችላል። ውሻው ከየት መጣ? የማን ነው? የታሰረ ነበር? የታመመ ነበር? ከውጭ የመጣው ሰው የበቀለ ወዳጅ ነው? ወዘተ... የእነዚህ አማራጭ እምቅ (potential) ሁኔታዎች በአንድ ጊዜና ቦታ ውስጥ ልፃፍ ስትል ሕፅን ይገባል። ሕፅን ወሽመጥ ማለት ነው።

ለ/ ሁለተኛው በአንድ አጋጣሚ አንድ ሬስቶራንት ውስጥ (ሆላንድ፣ ዴንሃግ ከተማ) እንጀራ ስበላ (ለብዙ አመታት አልበላሁም ነበርና) ለመጀመሪያ ጊዜ እንጀራ ልዩ እንደሆነ ተገለፀልኝ። ይሄንን አንዳንድ ሰዎች ኪነ-ጥበባዊ ተመክሮ (Artistic experience) ይሉታል። ከዛ ጥያቄዎች ጠየቅሁ። "የምበላው እንጀራ ከመበላት ውጭ ምን መልዕክት አለው?" ብዬ፡፡

ይሄን በሚመለከት የተገነዘብኩት ነገር እንጀራ የተለየ መሆኑ ነው። የተለየ የሚሆንበት ምክንያት አንዱ እንጀራ የሚሰራበት የጤፍ እህል ኢትዮጵያዊ መሆኑ፣ ሁለተኛ እንግዳ አምሳያ የሌለው ቅርፁና ሳያቋርጥ ለብዙ ሺህ ዘመናት በአገራችን ለምግብነት ማገልገሉ ነው። ለምን ሆነ? ይሄ አዲስ የጉሥዐተ ልብ (Discourse) መንገድ ቀዳጅ ነው። የሕፅናዊነት አእምሮአዊ ኑባሬው ይሄን ከመግለፅ ይጀምራል።

የጥንት ሰዎች ሙሉፅ የሆነ ሕይወት ነበራቸው። ማለት የሚያደርጉት፣ የሚያስቡትና የሚያመልኩት ሁሉ በአንድ ወጥ የፍልስፍናና የእምነት ሥርአት የታገገ ነው። ታዲያ እንጀራ ከምግብነቱ ሌላ ይሄን ተንተርሶ ምን ተጨማሪ መልዕክት (ሃይማኖታዊ፣ ማህበራዊ፣ ስነ ልቦናዊ፣ ታሪካዊ) ሊኖረው ይችላል? ለእኔ ይሄ "ዳቦ" ምን ያወራኛል? እንጀራ ራሱ ልክ እንደ መፅሃፍ ወይም እንደ ሃውልት ታሪክ ማስተለለፊያ ወይም የፍልስፍና ማስተላለፊያ ከሆነስ?

ብዙ ጊዜ ሰዎች ሃሳባቸውን በቋንቋ (በተረት)፣ በፅብነታ-ፅሁፍ፣ በብራና፣ በወረቀትና በእንጨት ላይ ታሪካቸውን ብቻ ሳይሆን ራዕያቸውንም ይፅፉሉ። ቦንስት የተባለ ኤሊየን ፊኖሚኖሎጂስት Things do not only exist but also act and have performative potential (ቁሶች ዝም ያለ ሕልውና ብቻ የላቸውም፣ እምቅ የግብር እና የተሳትፎ ሃይል አላቸው) ይላል። ከሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ጀምሮ ቁሶች ኮስተር ያለ የፍልስፍና ጥናት ውስጥ ከሰዎችና ከማህረሰቦች ባላነሰ መልክ እየተጠኑ ነው። ከዚያ ቀደም ብሎ (አሁንም) በአንትሮፖሎጂ፣ በኤትኖግራፊ የቁስ ባህል (Material culture) በሚባል አጠቃላይ አርዕስት ስር ሰፊ የምርምር ቦታ አላቸው (አከራካሪ ነገሮች ቢኖሩም)።

ታሪክ የሚጠናው ወይም የአንድ ህብረተሰብ ባህርይ የሚገመገመው ከመሬት ተቆፍሮ

> በሚወጣ ነገር ብቻ አይደለም። አሁን ባሉ ተቆፍረው ከሚወጡ ነገሮች የበለጠ ዕድሜ ባላቸው እንጀራን በመሰሉ ነገሮችም ነው። ይሄ የምበላው እንጀራ ቅርፁና ቅርፁ የተገነባባቸው ንጥረ ነገሮች ምን ሊያወጉኝ ይፈልጋሉ? ብዬ ስጠይቅ የምጀምረው ቁሱን ከመግለፅ ነው።

አንደኛ እንጀራ ክብ ነው፣ ሁለተኛ እንጀራ አይኖች/ቀዳዶች አለው (ትክክለኛው ቃሉ አይን ነው)፣ ሦስተኛ በፈሳሽና በጠጣር መሃል ያለ ነው። በእሳት የበሰለ ነው። በቀዳዳዎቹ አየር ይመላለሳል። አራቱ ባህርያተ ስጋ ተስማምተው ያሉበት ነው። እንጀራ ውብ ቅርፅ ብቻ ሳይሆን በቋንቋ ዘይቤ ውስጥ ተደጋግሞ የተነሳና ኑሮንና ሕልውናን ለመግለፅ ስራ ላይ የዋለ ነው። እንጀራ ጋገረ፣ እንጀራ ፈላጊ፣ የእንጀራ ገመዱ ተበጠሰ ወዘተ የመሳሰሉት ጥቂቶቹ ናቸው። ከዚህ ቀጥሎ የማደርገው ቁሱን በአጠቃላይ ከታሪክ፣ ከሚት፣ ከሲምቦሊዝም ከነገረ ትዕምርት (Semiotics) በማያያዝ ከቅርፅ ፀባዩ (Morphology) በላይ ምን እንደሚነግረን ለማሰስና ለመተርጎም መጣር ነው።

እንጀራ ታሪክ ውስጥ እንዲገባ ማለት መቼ ለመብል እንደዋለ መጠየቅ ትክክለኛ ነው። አነሳሱንም ማወቅ ልገለገልበት የፈለኩትን ትዕምርት ሊያዳብርልኝ ይችላል። አጀማመሩን የሚገልፅ ገድል እንደሚኖር ጠርጥሬአለሁ። ሲያጋጥመኝ ግን ትንሽ ሳይንሳዊ ሆነብኝ። በእርግጥ በአነሳሱ ውስጥ ተፎካካሪ ታሪክ አለ። ይሄ ተፎካካሪ ታሪክ ግን ለተረት ይቀርባል። የመሰለኝን ተአማኒነት ያለውን ገድል ላንሳ። ታሪኩ በብዙ ነጥብ የመለኮት ተፅዕኖ የማይገባበት ነው። ዘመናዊ ታሪክ ይመስላል።

ጤፍ እንጀራ የተፈጠረው ከክልበ 1500 ዓመታት በፊት በታላቁ የኢትዮጵያ ንጉስ በኢትኤል ወይም በሰንደቅ አላማ ጊዜ ነው። ኢትኤል ለመጀመሪያ ጊዜ ራሱን አፄ ብሎ የጠራ ንጉሠ-ካህን (God-King) ነው። ሃይማኖቱ አረማዊ ነበር። ዘውዱ ላይ የዘንዶ ምስል ስለሚያደርግ የዘንዶ ንጉስ ይባላል። በዛን ጊዜ ያሉ ነገስታት የዘንዶ ወይም የእባብ ቅርፅ ያለበት ዘውድ የሚደፉ ናቸው። የዘንዶ ሐይማኖቶች (Serpent religions) በጥንት ዘመን በብዙ የአለም ክፍሎች የሚታዩ የእምነት ክስተቶች ነበሩ። ታሪኩ እንደሚለው ሰንደቅ አላማ ንጉስና ካህን ብቻ ሳይሆን ተፈጥሮን መመራመር ይወድ ነበር። በዚህም ስራው እንደሚባለው ዘመሚትን፣ በቅሎንና የሜዳ አህያ የመሳሰሉትን እንስሳት በማዳቀል አዲስ ጥራት የፈጠረ ነው። የሚበላውና የሚጠጣው ከሰዎች የተለየና የራሱ አትክልትና ቤተ-እንስሳ እንደ ነበረው ይነገራል። 425 ዓመታት ምድር ላይ ከኖረ በሁዋላ መኖር ይሰለቸውና አንዲት ሴት እንድትገድለው ራሱን ያዘጋጃል። ይህቺ የገደለችው ሴት ኢተያ ትባላለች።

እሱን ገድላ ስትነግስ ሳባ ወይም ማክዳ ተባለች። በእሷ የንግስ ዘመን ረሃብ ይገባና ህዝቡን የምታበላው ታጣለች። ንግስት ከመሆኗ በፊት ዳንሰኛ ወይም የቤተመንግስት የኪነት ተወዛዋዥ ነበረች። በሕልምዋ ኢትኤል መቃብር (ማለት የዘንዶው ንጉስ) ጋ ሄዳ መቃብሩ ላይ የበቀለውን ሳር አጭዳ ማድረግ የሚገባትን አድርጋ ሕዝቧን እንድታበላ ተነገራት። ሰንደቅአላማ መቃብር ላይ የተገኘው ሳር ጤፍ ነበር። ጤፍ ማለት ጣፋጭና ብዙ ማለት ነው። በቀላሉ ጤፍ የምርምር ውጤት ነው።

> የሩቅ ዘመን ታሪክ ሲነሳ ለዛሬ ዘመን እንዴት ሊበጅ ይችላል? ብሎ ከማሰብ ይልቅ፣ ተረት ስለሆነ አይጠቅምም ብሎ ገና ከመነሻው የሚንቀው ይኖራል። በአለም ላይ ያሉ ብዙ ጎሳዎች በገድላቸውና በሚታቸው ሚያዘወትሩት ምግባቸው "ተሰጠን" የሚሉት ከአምላካቸው ነው። አንዳንዶቹ እንደውም "በዝርው የተፈጠርነው ሁልጊዜ ከምንበላው የእህል ዝርያ ነው" ይላሉ።

በእርግጥ ይሄን ታሪክ የጠቀስኩበት ምክንያት ከባዶ አለመነሳቴን ለማሳየት ብቻ ሳይሆን፤ ከ3500 ዓመታት በፊት የተፈጠረ ነገር ዛሬም ሊያገለግል የሚችልበት ምክንያት እንዳለም ለመፈተሽ ነው።

በአረማዊ ሃይማኖቶች አማልክቶች ብዙ ናቸው። የሚሰየሙትም በተፈጥሮ ውስጥ ባላቸው ቦታና ለሕዝብ በሚሰጡት ተጨባጭ አገልግሎት ነው። በኢትዮጵያ አረማዊ ሐይማኖቶች ውስጥ ፀሐይ ትልቅ ቦታ ነበራት። የምትወከልበትም ምስል ክብ ነበር። የፊደላችን ፀሐዩ ፀ (ፀሐዩ ፀ የሚባለው) አንዱ ምስክር ነው። ፀሐይ ሰማይ ላይ እንዳለች አይን ትቆጠር ነበር። የእንጀራን ቀዳዶች ዐይን የምንላቸው በነሲብ አይመስለኝም። ዐይን የሚፃፍበት ሆሄ ዐ መሆኑ (ዐይኑ ዐ) ቀላል ጉዳይ አይደለም። ክብና ክብነት በየትኛውም የአለም ክፍል የሙሉዕነት ተምሳሌት ነው። ፀሐይ የሕይወት ሰጪነት ተምሳሌትነት አላት። የእንጀራ ስፋትም አንጋጠን የምናየውን (በምሽት) ከዋክብት የፈሰሱበትን ሰማይ ይመስላል። በጥንት ግብፃውያን የፀሐዩ አምላክን ራን የሚወክለው ክብ ከመሃሉ አንድ ነቁጥ አለው። እንጀራ የሚለው ቃል መጨረሻ ላይ ያለው ሆሄ "ራ" ይሄን አምላክ የሚወክል ሊሆን ይችላል። በምሳሌነቱ በአለም ላይ ያለው ማንኛውንም አይነት ፍጡር የሚያገናኝ የመንፈስ ቀለምሲስ ወይም ሞገድ ነው። ክቡ ውስጥ ያለው ነጥብ የእንስትና የተባዕታይ ባሕርያት ወይም ስልጣናት እንደተዋሃዱ ማሳያ ነው። ይሄን ምስል ገፋ አድርገን ነጥቦቹን ብናበዛ ወደ እንጀራ ቅርፅ፣ ይሄም ሂደት ወደ ሰፋ ትርጉም እንድንቀሳቀስ ይገፋፋናል።

እላይ እንዳልኩት የክብ ተምሳሌትነቱ የማገናኘት (Connectivity) ጉዳይ ከሆነ እንጀራ የዚህ ፅነሰ ሃሳብ

ተጨባጭ የሆነ በሃይማኖት ቀኖናዎች መለዋወጥና እርስ በእርስ ከመጠፋፋታቸውና ከመበላለጣቸው ስልት አምልጦ የወጣ አለማዊ የመረጃ አሃድ ነው። ዘመናዊ ደራሲዎች በየትም አገር በተለያየ መልክ የአገራቸውን የጥንት ተረቶች ለድርሰቶቻቸው ቅርፅና ይዘት መስሪያ ተጠቅመውባቸዋል። ይሄ መሸጋገር (Transition) ብዙ ጊዜ ግን ከትረካ ወደ ትረካ ነው። ከድርሳን ወደ ድርሳን ነው። ከተረት ወደ ተረት ነው።

"ግራጫ ቃጭሎች" የተባለው የመጀመሪያ ረጅም ልብወለድ ስራዬ እዚህ ይመጣል። ይሄ መፅሐፍ ዋናውን ታሪክ በሚያጅቡ ንዑስ ታሪኮች፣ በህዳግ ማስታወሻዎች፣ በቁርጥራጭ መረጃዎች፣ በአንዳንድ የቁዘማ ውጤቶች አጀብ የተሰራ ነው።

ይሄ ቅርፅን ለማደን መጣር አይደለም። ሁልጊዜ በደቡላዊ (dualistic) ስልት ስለምናስብ እንጂ፣ ቅርፅና ይዘት የተናጠል ቦታ የላቸውም። እዛና እዚህ አይደሉም። አንድ ላይ የሚተገበሩ ናቸው። በፍልስፍናም ይሁን ሃይማኖቶቻችን በምድራሶቻቸው (Hermeneutics) ሁልጊዜ ባለቤትና ተሳቢ (subject-object) ክፍፍል ላይ ስለሚያተኩሩ ከዛ የተበደርነው ይሆናል።



> **እንጀራ ጠንካራ የልዋጭነት እሴት አለው (Metaphorical value)። ለመፃፊያ ሞዴልነት ለመጠቀም ይመቻል። ሞዴል ሲደረግ ከእንጀራነት ይላቀቅና ንፁህ ጂኦሜትሪ ይሆናል።**

ብዙ ጊዜ ሞዴሎች ከሚያጠኑት ጉዳይ የበለጠ ወይም የሚስተካከል ውስብስብነት ይኖራቸውና ራሳቸው መልሰው ችግር ይሆናሉ። እንጀራ ግን እንደ ሞዴል የቀላልነቱ ምክንያቶች እነዚህ ናቸው፤

1/ እንጀራ የተሟላ አይነት ውክልና አለው። ይታያል (እንደ ስዕል)፣ ይነካል፣ ይቀመሳል፣ እናም ይበላል። የመጨረሻው ፀባዩ የተለየ ያደርገዋል። እንደ ብዙ ቁሳቁስ በሩቅ የሚታይ አይደለም። ከሳብጀክቱ (የሰው ልጅ) ጋር ይዋሃዳል (embodied)።

2/ የትውስታም ሰሌዳ ነው። አርኪዮሎጂስቶች በጥንት ጊዜ የተሰራ ቁስ አግኝተው በመሳሪያቸው መርምረው የነዚህን ቁሶች ምንነታቸውን ያነባሉ። ተፎካካሪ ወይም የሚጋጭ ትርጉም ቢሰጣቸውም መረጃ ይሆናሉ። አፄ ሰንደቅአላማ የፈጠረው ጤፍ ተፎካካሪዎች የሚሻሙበት ዕላት (Icon) ነው። እንጀራ በሆነ መልክ ወገናዊነትን ያመልጣል። ተፎካካሪዎች ሁሉም ይሸቱታል። በልቶ የማያድር የለም። የድንጋይ ላይ ፅሁፎች ሲጠፉ፣ ሲቃጠሉ፣ ሲዘረፉ፣ ከቦታ ቦታ ተላልፈው ሲጠፉ፣ እንጀራን ማንም ሊያሸሸው ባለመቻሉ እዚህ ደርሷል። ብዙ ዘመን የኖረው ሰንደቅአላማ መቃብር ላይ መገኘቱ ረዥም ዕድሜ ከእሱ መዋሱ ምሳሌ ይሆን?

"እንጀራ ውስጥ ሚስጢር ሊኖር ይችላል" ካልኩ ሌላ ሚስጢሩ ምንድነው? እንጀራ እንደ አንድ መረጃ ማስተላለፊያ መሳሪያ መረጃ መዘከሪያ ሲሆን ምን እየተዘከረ ነው? ከአረመኔው ባህላችን ለትርጉም ፍተሻ እንጀራን ስነካካ የማገኘው ምንድነው?

<u>ሀ/ የንጥረ ነገሮቹ ጥቂትነት (ቀዳዳ፣ ቀዳዳ ያልሆነ ቦታና ክብነቱ)</u> - እንጀራን ቀርበን ስናየው የዐይኖቹ ቅርፅ ስድስት ጎኖች ያለው (hexagon) ነው። ይሄ ቅርፅ ሕይወት ባላቸውና በሌላቸው ሕዋሳትና ሞሎኪዉሎች አገነባብ ውስጥ የምናገኘው ነው። ይሄ ሁለንተናዊ ቅርፅ ተምሳሌትነቱን ያጎላዋል። በተጨማሪም የነዚህ ዐይኖች ስርጭት በጂኦሜትሪ ፍራክታል (fractal) ይባላል። ፍራክታል በአጭሩ እንብር የለሽ በሆነ ስልት አንድ የጆሜትሪ ቅርፅ ራሱን ሲደጋግም ማለት ነው።

ሁለትአይነት ፍራክታሎች አሉ። አንደኛው ርትዕ ፍራክታል ሲባል ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉት ብዙዎቹ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መስቀሎች ናቸው።



ርትዕ የተባሉበት ምክንያት ሆነ ተብለው በዕቅድና በስሌት ስለተሰሩ ነው። ሁለተኛው ኢርትዕ ፍራክታል ሲሆን የእንጀራ አይኖችን የሚመለከት አይነት ስርጭት ነው።



<u>ለ/ እነዚህ ቀዳዳዎች የሚገናኙበት ሰፊ የቱቦ ስርአት መኖሩ፡-</u> ግን እንጀራ ባለ ሶስት አውታር በመሆኑ ከውስጡ ዐይኖቹ የሚገናኙበት የአሸንዳ ስርአት አለው ይሄም ኢርትዕ ነው። ይሄ የአሸንዳ ስዕል ወደ የወጥመድ ጠልሰም (labyrinth or maze) ፅነሰ ሃሳብ ይወስደናል።

ስለ ሶስት አይነት ወጥመዶች ላንሳ። አንደኛው የአንድ አቅጣጫ ወጥመድ ሲሆን አንድ መነሻና አንድ መድረሻ ያለው ነው። ይሄ በልብወለድ አፃፃፍ ተምሳሌትነቱ ክላሲካል ወይም ብሉይ የምንለው ነው፤ ጂኦሜትራዊ ንፅፅር እንጠቀም ካለን መስመራዊ ነው። ይሄ ምስል/ ጠልሰም ጥንታዊ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥም ክታቦች ላይ እናገኘዋለን።



ሁለተኛው ወጥመድ አንድ መነሻና ብዙ አማራጭ ጎዳናዎች ስላሉት ልብወለድ ይነግረናል። አጋጣሚ፣ ምናልባታዊነት፣ ዕጣ ፈንታ፣ ቀውስ ይከሰቱበታል፣ ይላፉበታል። ብዙ ጊዜ ዘመናዊ በተባሉ ልብወለዶች ውስጥ የሚከሰትና የሚወክላቸው ጠልሰም ነው።



ሶስተኛው የወጥመድ ምስል በብዙ ቀዳዳ ገብቶ በብዙ ቀዳዳ የመውጣትን ሁኔታ ነው። ይሄ የሕፅናዊነት ቦታ ይመስለኛል።



4/ የአንድ እይታ መስክ ውስጥ መሆኑ (a single visual field)

5/ ሁሉ ሰው የሚያውቀውና በቀላሉ ሊወዳጀው የሚችል ተጨባጭ ቁስ እንጂ ረቂቅ ፅንሰ-ሃሳብ አለመሆኑ።

በትርጉም ደረጃ ከነዚህ እላይ ካነሳሁዋቸው ጉዳዮች ያወጣሁዋቸውና ልመራባቸው የመደብኩዋቸው የሕፅናዊነት ስነግብር ንጥረነገሮች እነዚህ ናቸው:-

1/ ሁሉ ነገር በታቀደና ባልታቀደ ግኑኝነት ውስጥ መሆኑን፣
2/ ሁሉ ነገር በታቀደና ባልታቀደ ግኑኝነት ብቻ ሳይሆን በታቀደና ባልታቀደ ለውጥ ውስጥ መሆኑ፣
3/ አሁን ተነጣጥሎ የተቀመጠ የሚመስለው ቢያንስ አንድ የጋራ የግኑኝነት መስመር እንደሚያጣ (ከአዳምና ከሄዋን ተገኘን ማለት) (ሞሎኩሌው ወይም የፀሐይ ስርአት ከአንድ ታላቅ ፍንዳታ (Big bang) ተፈጠረ  እንደማለት)፣
4/ አንድ ወጥ አጭር ታሪክን ወይም ረዥም ልብወለድን "የተሳካ" ማለት ጎዶሎውን መቀበል መሆኑን።

ለአባባል ሕፅናዊነት ሁሉን ነገር ቀናንሰን ስናነበው ግኑኝነት ነው። ዋናው የስነፅሁፍ አላባው ይሄ ነው። እንጀራ ውስጥ የተቀበረው ሚስጢር ይሄ ነው። ከላይ ሲያዩህ ነጣላህን ያለህ ይመስልሃል ግን አነሰም በዛም፣ አወቅሁትም አላወቅሁትም፣ ገባኝም አልገባኝም፣ ተከሰተ አልተከሰተ መረብ ውስጥ ነኝ ማለት ነው።

ጂኦሜትሪና ልብወለድ አፃፃፍ ያላቸው ግኑኝነትና ትርጉም ስለሳበኝ ንባቤን በመጠኑ አሰፋሁና ይሄን በሚመለከት የተደረጉ ነገሮች እንዳሉ ለማጥናት ልሞክር ብል ከመጀመሪያው መጀመር ግድ ይላል። ከላይ እንዳልኩት ያለሁበት የግል ሁኔታ የተለየ ነው። ከጀርባዬ ሰፊ የድርሳን ትንታኔ፣ ረቂቅ የሂስና የፍልስፍና ባህል የለም። ያን አድካሚ ጉዞ ካላሳለፈ ህብረተሰብ ነው የወጣሁት። በግልም ደረጃ በሁሉም አቅጣጫ ሊያስኬደኝ የሚችል የፍልስፍና ዕውቀት ያጥረኛል። እኔ የመጣሁት ከጉዳዩ ጀርባ ነው። ይህ ማለት በመከወን ሂደት ውስጥ ካጋጠመኝ ጥቅንጥቅ እንጂ ከትወራ ጥናት አልተነሳሁም። ያለሁበትን ሁኔታ በቲዮሪ ለመረዳት ስሞክር ካደረኩት ትንሽ ልፋት የተረዳሁት ጓታሪና ደሉዝ "ካፒታሊዝምና ስኪዞፌርንያ" (Capitalism and Schizophrenia) በተባለው መፅሃፋቸው ከጠቀሱት "ራይዞም" ከተባለው ሞዴላቸው (የማህበረሰብና የዕውቀት ሞዴል) ጋር ተመሳሳይ መሆኑ ነው። ራይዞምን "የሃሳብ ምስል ነው" ይሉታል። በተለይ የኢንተርኔት መምጣት የዚህን ፅነሰ-ሃሰብ ቦታ ከፍ አድርጎታል። በብዙ በኩል ሕፅናዊነት ከዚህ የሚመሳሰል ሆኖ ሳለ፣ ራይዞም ተዋረድን (Hierarchy) ቦታ ባለመስጠቱ የሚለይ ይሆናል። በተለይ እ.ኤ.አ ከ90ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ጀምሮ ተፅኖ ማሳደር የጀመረው በይነ-ዲሲፕሊያዊው ኢኮሎጂካል ትወራ የግኑኝነትን ቸል መባል ፍቆታል።

የሕፅናዊነት አንዱ አጀንዳ በመስመር ሳይሆን በመረብ ስልት የማሰብ ነው። ይሄ ሰለጠኑ በተባሉ አገሮች እንግዳ ላይሆን ይችላል። የትራንስፖርት፣ የኤሌክትሮኒክስ ቴክኖሎጂ መርቀቅና የመረጃ መረቦች መንሰራፋት እንግዳ አያደርጉትም። እንደኛ ባለ ቴክኖሎጂ ባልዳበረበት ሕብረተሰብ ውስጥ ይሄን ማንሳት ነገሩ ሳይመጣ ትንሽ መቅደም ይመስላል። ግን አይደለም። የኢትዮጵያ ህዝብ አንድ አካባቢ ለብዙ ሺህ ዘመናት የኖረ ነው። መረቡ ትራንስፖርትና ኤሌክትሮኒክስ ባይሆንም ጀነቲክ፣ ቋንቋ፣ ጦርነትና የንግድ ግኑኝነት ነው::

አለም በአብዛኛው የተገነባው አብሮ በመስራት (Collective intelligence) ነው። ለምሳሌ ስክሪፕቶህን አንስተህ የመጣችበትን ሂደት በምናብህና በማስረጃ ብትከታተል እጅግ ውስብስብ፣ የብዙ ሰዎች እውቀትና ጉልበት የገባበት እንደሆነ ትረዳለህ። ለመሆኑ አንድ ተባዕት ወፍና እንስት ወፍ ጎጆ ቢሰሩ፣ የጎጆውን ስንደዶዎች በመምዘዝ ማን የትኛውን እንደሰካው ወይም እንደ ደወረው ማወቅ እንችላለን? ይሄን በሚመለከት የሰው ልጅ ከእስክሪፕቶው ወይም ከወፎቹ የተለየ አይደለም።

በሌላ በኩል ደሞ ሕፅናዊነት እስከዛሬ ከለመድናቸው የተለዩ የሂስ ስራዎችን እንድናዳብር ይገፋፋናል። በቋንቋ ብቻ ከማጥናት በምስልና በአሃዝ ማጥናትና መተቸት ያስችለናል። ለምሳሌ በመረብ ካርታ (Network mapping) ወይም በአክተር ኔትወርክ ቲዮሪ ቋንቋ

ውስብስብ ካርታዎች (Complexity mapping) በመስራት ወይም በዲስኮርስ አናሊስስ ካርታ (Discourse analysis mapping) አልፎ ተርፎም በአሃዝ ማስላት እንድንችል ይገፋፉናል። ከቃላት ዘልቆ የገፀባህርያት ቦታ (Space) በነዚህ ዓይነት ውስብስብ ጠልሰሞች ሊታይ፣ ሊገለፅና ሊገመገም ይችላል።

ቱብዬነት፦ በ'ፌስ ቡክ' በትጋት ከአድናቂዎቹ ጋር የሚገናኝ ብቸኛ ደራሲያችን መሆንህ ይታወቃል። ከዚያ ባለፈ ከአንባቢዎችህ በአጠቃላይ የምታገኘው ግብረ መልስ ምን ይመስላል? በአንተና በስራዎችህ እየተቀረጸ ያለ አዲስ የአንባቢያን ትውልድ አለ ብለን ብናምን ትስማማለህ?

በአሁኑ ወቅት ለምሰራው ስራ መረጃ ስለምፈልግ ብዙ ጊዜ ኢንተርኔት ላይ ነበርኩ። የግጥም ባሕር፣ የመጣጥፍ ሃይቅ በዛ አለ። ፌስ ቡክ በመጠቀም ብቸኛ ደራሲ መሆኔን እናንተ "አብሮነቶች" ናችሁ የነገራችሁኝ። "ፍሬንዶች" ለሚያቀርቡልኝ አንዳንድ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ግን ብዙ ጊዜ አረፍዳለሁ። ከእኔ ይልቅ የአገራችንን ስነ-ፅሁፍ ወደ መርበትብተ-ኤሌክትሮኒክ ያመጡት ወጣቶች ሊመሰገኑ ይገባል። የእነሱ የድርጊት ሕልውና ስለሚቀድም ልፋታቸው የገነነ ነው። ስለራሴም እንዳውቅ ገፋፍተውኛል። ልክ እንደ ጠንቋይ፣ ደራሲ ስለራሱ አያውቅም። ምናልባት ወጣቶቹ የበዙት "ደራሲያን ማንሳት ይገባቸዋል" የሚሏቸውን እስከዛሬ የተሳቱ ጉዳዮች ስላነሳሁ ይሆናል፤ ወይም ገና ወጣትነቴ አልከሰመምና (እስከ አሁን ድረስ ከምኑም ከምኑም እየተላተመ መጥቶ ከተረፈ፤ በተአብነት ይመዘገባል)- እኔን የሚመዘምዘኝ ጉዳይ እነሱንም ይመዘምዝ ይሆናል። እነዚህ ግምቶቼ ናቸው። በግምት ደ'ሞ እርቀት አይኬድም።



ቱብዬነት፦ አስገራሚ፤ አስቂኝና ያልተለመደ የምትለው አጋጣሚ ካለ?

በብዙ ነገር ተገርሜ የጨረስኩ ይመስለኛል። ድሮ የገረሙኝ ነገሮችን ዛሬ ሳስባቸው ለዛሬ አስገራሚ ሆነው አይታዩኝም። የሚያስቅ? ሉል (lol) ከመጣች ጀምሮ መንተክተክ ሳይቀንስ አልቀረም? (ለማሾፍ ይፈቀድልኛል?)



ከደራሲ አዳም ረታ ጋር ያደረግነው ውብ ውይይት ከሞላ ጎደል ይህንን ይመስል ነበር። ድንቃይ የጥበብ ስራዎቹን ለማንበብ ዕድሉን ያላገኛችሁ መፅሃፍቶቹን አግኝታችሁ እንድታነቡ እያበረታታን፤ በቅርቡ ለህትመት የሚበቃ፤ በሚሊዮን አንባቢዎቹ ዘንድ በጉጉት የሚጠበቅ "የስንብት ቀለማት" የተሰኘ ረጅም ልቦለዱ የተዋጣ እንዲሆንለት ከልብ እንመኛለን።